ዘቴዎዶጦስ ፡ ም ፡ ፶፫ ።

፲፩፤ ወንነግረከ ፡ ወናሌብወከ ፡ ዘንተ ፡ ስመ ፡ ዘውእቱ ፡ ወልድ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፩ዱ ፡ ህላዌ ፡ ምስለ ፡ አብ።

፲፪፤ ወባሕቱ ፡ ንትመየጥ ፡ ኀበ ፡ መካን ፡ ዘአቅደምነ፡ ወጢኖቶ ፡ ወንትናገር ፡ በእንተ ፡ አስተርእዮቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዘተወልደ ፡ ለነ ፡ ዮም ፡ በሥጋ፡ ወንከሥቶ ፡ ለከ ፡ በምሳሌ ፡ ዘከመ ፡ እፎ ፡ ዘኢያስተርኢ ፡ በህላዌሁ ፡ አስተርአየ ፡ ይእዜ ፡ ወዘኢይትገሠሥ ፡ በእንተ ፡ ዘኢኮነ ፡ ህላዌ ፡ ሥጋ ፡ ተገሠ፡ ይእዜ ፡ በሥጋ ። ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፩ ። ሉቃ ፡ ፳፬፡ ፴፱ ። ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፲፮ ።

፲፫፤ ናሁ ፡ ቃልነ ፡ ለእጓለ ፡ እመሕያው ፡ ዘይወፅእ ፡ እምአፉነ ፡ ወንትናገር ፡ ቦቱ ፡ በበይናቲነ ፡ ኢይክል፡ መኑሂ ፡ ይርአዮ ፡ እስመ ፡ ለቃል ፡ አልቦቱ ፡ ሥጋ ወኢይትከሠት ፡ ወኢለመኑሂ ፡ ወኢይትገሠሥ ፡ በአእዳው ፡ አላ ፡ ሶበ ፡ ይጸሐፍ ፡ ቃል ፡ በክርታስ፡ ወይከውን ፡ ሎቱ ፡ መልክዕ ፡ አሚሃ ፡ ይከውን ፡ ክሡተ ፡ ወያስተርኢ ፡ ወይትገሠሥ ።

፲፬፤ ወለእመቦ ፡ ብእሲ ፡ ዘይፈቅድ ፡ ይጽሐፍ ፡ መጽሐፈ ኀበ ፡ ካልኡ ፡ እስመ ፡ ቃል ፡ ዘኢይትረአይ ፡ ወዘኢይትገሠሥ ፡ ሶበ ፡ ይጽሕፎ ፡ ዝኩ ፡ ብእሲ ፡ ውስተ ፡ ክርታስ ፡ አሚሃ ፡ ትሬእዮ ፡ ዘኢትክል ፡ ርእዮቶ ቅድመ ፤ ወለመልክዐ ፡ ቃል ፡ ዘኢትክል ፡ ገሢሶቶ፡ ቅድመ ፡ ትገሥሥ ፡ ይእዜ ፡ በክርታስ ፡ በጽሕፈት ፡ እስመ ፡ ለቃል ፡ አልቦቱ ፡ ሥጋ ፡ ወሶበ ፡ ተጽሕፈ ፡ በክርታስ ፡ ወበመልክአ ፡ ጽሕፈት ፡ ደለወከ ፤ አሚሃ ፡ ትርአዮ ፡ ወትግሥሶ ፡ ወናሁ ፡ ይእዜ፡ ኮነ ፡ ምሳሌ ፡ ብሩሃ ፡ ወብዑነ ።

፲፭፤ ወአዘከርናከ ፡ ዘኮነ ፡ በምሳሌ፡ ዘልማድ ፡ ዘይከውን ፡ ወይሄሉ ፤ ወንሕነ ፡ ናጤይቀከ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዋሕድ ፡ ቀዳማዊ ፡ እምቅድመ ፡ ኵሉ ፡ አዝማን ፡ ዘአልቦቱ ፡ ሥጋ ፡ በህላዌሁ ፡ ቀዳማዊ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ ለብሰ ፡ ድኅረ ፡ ህላዌ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው፡ ወተወልደ ፡ እምቅድስት፡ድንግል ፡ ወአልቦቱ፡ ጥንት፡ ለህላዌ ፡ መለኮቱ ።

፲፮፤ ወኢትስአለኒ ፡ ዘከመ ፡ እፎ ፡ ልደቱ ፡ ለወልድ ፡ ዋሕድ ፡ እምአብ ፡ ወዘከመ ፡ እፎ ፡ ልደቱ ፡ እምድንግል ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ተወልደ ፡ እምአብ ፡ በህላዌሁ ፡ ወተወልደ ፡ እምቅድስት ፡ ድንግል ። በሥርዓት ፡ ዘሠርዐ ፡ ለርእሱ ፤ ውእቱ ፡ አምላክ፡ ወውእቱ ፡ ሰብእ ።

ዘቴዎዶጦስ ፡ ም ፡ ፶፫ ።

፲፩፤ ይህንንም ፡ ስም ፡ ከአብ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ እንደሆነ ፡ እንነግርሃለን ፡ እናስረዳሃለን ፤ ይኸውም፡ ወልድ ፡ መባል ፡ ነው ።

፲፪፤ ነገር ፡ ግን ፡ አስቀድመን ፡ የጀመርነውን ፡ የሥጋዌውን ፡ ነገር ፡ ወደመናገር ፡ እንመለስ ፤ ዛሬ፡የተወለደልን ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በሥጋ ፡ የመገለጡንም ፡ ነገር ፡ እንናገር ፤ በባሕርይ ፡ አይታይ ፡ የነበረውም ፡ እንደምን ፡ ዛሬ ፡ እንደታየ ፤የሥጋ ባሕርይ ፡ ስለሌለው ፡ የማይዳሰስ ፡ የነበረውም፡ እንደምን ፡ ዛሬ ፡ በሥጋ ፡ እንደ ፡ ተዳሠሠ ፡ በምሳሌ፡ እናስረዳሃለን ። ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፩ ። ሉቃ ፡ ፳፬ ፡ ፴፱። ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፲፮ ።

፲፫ ፤ ከአንደበታችን ፡ የሚወጣ ፡ እርስ ፡ በርሳችን ፡ የምንናገርበት ፡ የእኛ ፡ ቃል ፡ አለ ፤ ማንም ፡ ማን ፡ ሊያየው ፡ አይችልም ፤ ለቃል ፤ ግዘፍ ፡ የለውምና፤ለማንም ፡ ለማን ፡ አይታይምና ፡ በእጅም ፡ አይዳሠሥምና ፡ ቃል ፡ በብራና ፡ በተጻፈ ፡ ጊዜ ፤ ቅርጽም፡ በሆነለት ፡ ጊዜ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ የተገለጠ ፡ ይሆናል ፤ ይታያል ፤ ይዳሰሳል ፡ እንጂ ።

፲፬፤ ለወዳጁ ፡ መጽሐፍ ፡ ሊጽፍ ፡ የሚወድ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ቃል ፡ የማይታይ ፤ የማይዳሠሥ ፡ ነውና ፡ ያ ፡ ሰው ፡ በብራና ፡ በጻፈው ፡ ጊዜ ፡ ቀድሞ ፡ ልታየው ፡ የማትችለውን ፡ ያንጊዜ ፡ ታየዋለህ ፤ ቀድሞ፡ ልትዳሥሠው ፡ አይቻልህ ፡ የነበረውን ፡ የቃልን ፡ አካል ፡ ዛሬ ፡ በብራና ፡ በጽሕፈት ፡ ትዳሥሠው ፡ አለህ ፤ ለቃል ፡ ግዘፍ ፡ የለውምና ፤ ጽሕፈት ፡ በሚያስገኘው ፡ መልክ ፡ በተጻፈ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ያንጊዜ ልታየው ፡ ልትዳሥሠው ፡ ተገባህ ፤ እነሆ ፡ አሁን፡ ምሳሌው ፡ የተለየ ፤ የተረዳ ፡ ሆነ ።

፲፭፤ በተለመደ ፤ በሚደረግ ፤ ሲደረግ ፡ በሚኖር ፡ ምሳሌ ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ የቃልን ፡ ነገር ፡ አስረዳንህ፡ ከዘመን ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ የነበረ ፡ ቀዳማዊ ፡ባሕርዩ ፡ እንደ ፡ አብ ፡ ሥጋ ፡ ያልነበረው ፤ አንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ የሰውን ፡ ባሕርይ ፡ እንደ ፡ ተዋሐደ፤ ከቅድስት ፡ ድንግልም ፡ እንደ ፡ ተወለደ ፤ ለባሕርየ፡ መለኮቱም፡ ጥንት፡ እንደሌለው፡ እኛ፡ እናስረዳሃለን ።

፲፮፤ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ከአብ ፡ መወለዱ ፡ እንዴት እንደ ፡ ሆነ ፤ ከቅድስት ፡ ድንግልም ፡ መወለዱ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አትጠይቀኝ ፤ እርሱ ፡ በባሕርዩ ፡ ከአብ ፡ ተወልዶዋልና ፡ ለራሱ ፡ በአደረገው ፡ ተዋሕዶም ፡ ከድንግል ፡ ተወልዶዋልና ፡ አምላክ፡ ነው ፤ ሰውም ፡ ነው ።

ዘኤጲፋንዮስ ፡ ም ፡ ፶፩ ፡

፮፤ ወሶበ ፡ ተፈጸሙ ፡ እሉ ፡ ትንቢታት ፡ ወካልአንሂ እምኢሳይያስ ፡ ወኤርምያስ ፡ ወኵሎሙ ፡ ነቢያት ፡ እለ ፡ ተነበዩ ፡ ከመ ፡ ሀለዎ ፡ ይትወለድ ፡ አምላክ ፡ ቃል ፡ እምድንግል ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ኤርምያስ ፡ ነቢይ ፡ እንዘ ፡ ውእቱ ፡ ሰብእ ፡ መኑ ፡ ይክል ፡ ያእምሮ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ነሥአ ፡ ሥጋ ፡ እምእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ዘእንበለ ፡ ዘርዓ ፡ ብእሲ ። ኤር ፡ ፲፯ ፡ ፱ ።

፯፤ ፈጠረ ፡ ሎቱ ፡ ዘንተ ፡ ሥጋ ፡ ቅዱሰ ፡ ዘተወልደ ፡ እምብእሲት ፡ በከመ ፡ ተብህለ ፡ ወነሥአ ፡ ዘዚአነ ፡ ወበእንተ ፡ ዘዚአነ ፡ ይቤ ፡ አምላኪየ ፡ ዘውእቱ ፡ አምላክክሙ ፡ ገላ ፡ ፩ ፡ ፩ ።

፰፤ ወበእንተ ፡ ህላዌ ፡ መለኮትሰ ፡ ይቤ ፡ አቡየ ፡ ወበእንተ ፡ ጸጋ ፡ ዘጸገወ ፡ ለአርዳኢሁ ፡ ይቤ ፡ አቡክሙ ፡ ወበእንተ ፡ ህላዌ፡አርዳኢሁሰ፡ ዘይትማሰል በህላዌ ፡ ትስብእቱ ፡ ይቤ ፡ አምላኪየ ፡ ዘውእቱ ፡ አምላክክሙ ።

፱፤ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ውእቱ ፡ አቡሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በህላዌ ፡ መለኮቱ ፡ ወውእቱ ፡ አቡሆሙ ፡ ለአርዳኢሁ ፡ በጸጋሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ አምላኩ ፡ ለወልድ ፡ ውእቱ ፡ በእንተ ፡ ትስብእቱ ፡ ወአቡሁ ፡ በእንተ ፡ መለኮቱ ፡ ቀዳማዊ ።

፲፤ ዘኢይትነገር ፡ ልደቱ ፡ እምኔሁ ፡ በአማን ፡ አቡሁ ፡ ውእቱ ፡ እስመ ፡ አልቦቱ ፡ ጥንት ፡ ወኢተፍጻሜት ፡ በመለኮቱ ፡ ወደለወ ፡ ይእዜ ፡ ከመ ፡ ይበል ፡ አምላኪየ ፡ በእንተ ፡ ምጽአቱ ፡ ኀቤነ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቡሁ ። ዮሐ ፡ ፲፮ ፡ ፳፯—፳፱ ።

፲፩፤ እምቅድመ ፡ ዓለም ፡ ወለዶ ፡ አብ ፡ ለቃል ፡ ዘአልቦቱ ፡ ጥንት ፡ ወኢተፍጻሜት ፡ ወበደኃሪ ፡ መዋዕል ፡ ተወልደ ፡ በሥጋ ፡ እምእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ንጽሕት ፡ ዘእመንፈስ ፡ ቅዱስ፡

ክ ፍ ል ፪ ።

፲፪፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ኤጲፋንዮስ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ዘቆጵሮስ ፡ ጽሑፍ ፤ እስመ ፡ ሕፃን፡ ልሕቀ ፡ ወጸንዐ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እስመ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኮነ ፡ ይልሕቅ ፡ በበሕቅ፡ በአካል ፡ ወበጥበብ ። ሉቃ ፡ ፪ ፡ ፴፭ ፡ ፶፪ ።

ዘኤጲፋንዮስ ፡ ም ፡ ፶፩ ፡

፮፤ እሊህ ፡ ትንቢቶች ፡ አምላክ ፡ ቃል ፡ ከድንግል ፡ ይወለድ ፡ ዘንድ ፡ ትንቢት ፡ ከተናገሩ ፡ ከኢሳይያስ ፤ ከኤርምያስ ፡ ከነቢያትም ፡ ሁሉ ፡ የተናገሩት፡ ነገሮች ፡ ከተፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ ሰው ፡ ሲሆን ፡ ማን ፡ ሊያውቀው ፡ ይችላል ? ብሎ ፡ ኤርምያስ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ያለ ፡ ዘርዓ ፡ ብእሲ ፡ ከእመቤታችን ፡ ከቅድስት ድንግል ፡ ማርያም ፡ ሥጋን ፡ ነሣ ። ኤር ፡ ፲፯ ፡ ፱ ።

፯፤ ይህን ፡ ንጹሕ ፡ ሥጋ ፡ ራሱ ፡ ሊዋሐደው ፡ ፈጠረና ፡ እንደ ፡ ተነገረም ፡ ከድንግል ፡ ተወለደ ፤ ባሕርያችንንም ፡ ገንዘብ ፡ አደረገ ፤ የእኛንም ፡ ባሕርይ ፡ ስለተዋሐደ ፡ አምላኪየ ፡ አለ ፤ ይኸውም ፡ አምላካችሁ ፡ ማለት ፡ ነው ። ገላ ፡ ፩ ፡ ፩ ።

፰፤ የባሕርይ ፡ ልጁ ፡ ስለሆነ ፡ አቡየ ፡ (አባቴ) ፡ አለ ፤ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ስለሰጣቸው ፡ ልጅነትም ፡ አቡክሙ ፡ (አባታችሁ) ፡ አለ ፤ ባሕርየ ፡ ትስብእትን፡ ስለሚመስል ፡ ባሕርየ ፡ አርድእት ፡ አምላኪየ ፡ አለ፡ ይኸውም ፡ ፈጣሪያችሁ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፱ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ለጌታችን ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ አባቱ ፡ ነው ፡ ለሐርያት ፡ ግን ፡ በሰጣቸው ፡ ጸጋ ፡ አባታቸው ፡ ነው፡ ሰው ፡ ስለሆነ ፡ ለወልድ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ አምላኩ ፡ ነው ፤ ስለቀዳማዊ ፡ ባሕርዩም ፡ አባቱ ፡ ነው ።

፲፤ ከእርሱ ፡ የተወለደውም ፡ ልደት ፡ የማይመረመር ፡ ነው ፤ በእውነት ፡ የባሕርይ ፡ አባቱ ፡ ነው ፤ በመለኮቱ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ተገኘ ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያልፋል፡ አይባልምና ፤ ግን ፡ ከባሕርይ ፡ አባቱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አንድነት ፡ ሳይለይ ፡ ወደእኛ ፡ አንድነት፡ ስለመጣ ፡ ዛሬ ፡ አምላኪየ ፤ ሊል ፡ ተገባው ። ዮሐ፡ ፲፮ ፡ ፳፯—፳፱ ።

፲፩፤ አብ ፡ ጥንት ፤ ፍጻሜ ፡ የሌለው ፡ ቃልን ፡ ዓለምን ፡ ከመፍጠሩ ፡ አስቀድሞ ፡ ወለደው ፤ በኋላ ፡ ዘመንም ፡ በግብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ንጽሕት ፡ ከምትሆን ፡ ከእመቤታችን ፡ ከቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ በሥጋ ፡ ተወለደ ።

ክ ፍ ል ፪ ።

፲፪፤ ዳግመኛም ፡ የቆጵሮስ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ይህ ፡ ቅዱስ ፡ ኤጲፋንዮስ ፡ ሕፃኑ ፡ እንደ ፡ አደገ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ እንደጸና ፡ ተጽፏልና ፡ አለ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በአካልም ፤ በጥበብም፡ በየጥቂቱ ፡ ያድግ ፡ ነበርና ። ሉቃ ፡ ፪ ፡ ፴፭ ፡ ፶፪ ።

## ዘኤጲፋንዮስ ፡ ም ፡ ፶፩ ።

፲፫ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ በነቢይ ፡ እስመ ፡ እምቅድመ፡ ያእምር ፡ ሕፃን ፡ ሰምየ ፡ አቡሁ ፡ ወእሙ ፡ ይነሥእ ፡ ኀይለ ፡ ደማስቆ ፡ ወምሕርካ ፡ ሰማርያ ። ኢሳ ፡ ፰ ፡ ፬ ።

፲፬ ጠቢብ ፡ ዘይሜህር ፡ ለሰብእ ፡ አእምሮ ፡ ወተከለ ፡ አዕዛነ ፡ ለሰብእ ፡ ወአሠነየ ፡ ንባበ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ወረሰየ ፡ ልሳነ ፡ በሐማግ ፡ ርቱዐ ፡ ተዐገሠ ፡ ዘንተ ፡ ኵሎ ፡ ግብራተ ፡ በእንቲአነ ፡ ከመ ፡ ይዕቀብ ፡ ዘንተ ፡ ሥርዓተ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ውእቱ ፡ ዘሠርዐ ፡ በእንቲአነ ። መዝ ፡ ፺፬፡(፺፫)፡፰-፲። ማቴ ፡ ፲፪ ፡ ፳፪—፳፬ ።

፲፭ ኢያማስነ ፡ ምንትኒ ፡ እምአምሳለ ፡ ጽድቅ ። ወእምስምዓትኒ ፡ ዘአስተጋባእናሆሙ ፡ ወአኀበርናሆሙ ፡ እመጻሕፍት ፡ ቅዱሳት ፡ ወአእመርነ ፡ እምኔሆሙ ፡ ሠናየ ፡ ወአዋረይናሆሙ ፡ እንበለ ፡ ትርጓሜ ኢይኩን ፡ አምሳለ ፡ በእለ ፡ ይትዋሥኡነ ፡ ከመ፡ ይትቃረንዋ ፡ ለጽድቅ ። ዮሐ ፡ ፲፱ ፡ ፴፩ ።

፲፮ ወንነጽር ፡ ለለ፩ዱ ፡ ቃል ፡ እምቃላት ፡ ወኀይለ ፡ ዘውስቴቶሙ ፡ ወንትናገር ፡ ዳግመ ፡ ምክንያተ ፡ ነገር ፡ ዘይቤልዎ ፡ ዘከመ ፡ ትስብእቱ ፡ ናሁ ። ዮሐ፡ ፰ ፡ ፴፱ ።

፲፯ ናሁ ፡ አቅደምነ ፡ ወተናገርነ ፡ ባህሎ ፡ ዘይቤ ፡ አምላኪየ ፡ ዘውእቱ ፡ አምላክክሙ ፡ ብዙኃ ፡ ጊዜያተ ፡ ከመ ፡ ይለቡ ፡ ዘአልቦቱ ፡ አእምሮ ፡ ፍናወ ፡ ፩ዱ ፡ ቃል ፡ ወዘተብህለ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ሰብእ ፡ ወአልቦ ፡ ዘየአምሮ ።

፲፰ ወበዝንቱ ፡ ቃለ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ይትዐወቅ ከመ ፡ ውእቱ ፡ እም፪ቱ፡ዘያስተርኢ፡ወዘኢያስተርኢ ፩ዱ ፡ ሕላዌ ፡ በእንተሰ ፡ ዘያስተርኢ ፡ ይቤ ፡ አምላኪየ ፡ ወበእንተ ፡ ዘኢያስተርኢ ፡ ይቤ ፡ አቡየ ።

፲፱ ወአልቦ ፡ ዘይክል ፡ መኑሂ ፡ ያውሥእ ፡ ቃለ ፡ በእንተ ፡ እሉ ፡ ፪ቱ ፡ ሥርዓታት ፡ እፎኑ ፡ ውእቱ ፡ ሰብእ ፡ ዘኢኮነ ፡ ፍጡረ ፡ ወለእመ ፡ ኢኮነ ፡ ሰብአ፡ እፎመ ፡ ተሰምየ ፡ ሰብአ ።

፳ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ዘይትወለድ ፡ ይትከሠት ፡ ስሙ ፡ እምዘወለድዎ ፡ ወእምአዝማዲሁ ፡ ወሰብኡ ፡ ወነገዱ ፡ ወቅሩባኒሁ ፡ ወሰብአ ፡ ሀገሩ ፡ ወኢይደሉ ፡ ይትፈጸም ፡ ዝንቱ ፡ በብእሲ ፡ ሕጹጽ፡ አላ፡ ለዝንቱሰ ፡ ይበጽሕ ፡ ወይትፌጸም ፡ ለቃለ ፡ እግዚአብሔር ።

፳፩ ወሰበዚ ፡ ተብህለ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ በአማን ፡ ሰብእ ፡ ወመኑ ፡ ይክል ፡ ያእምሮ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ተሰምየ ፡ አብሲማዳኮስ ፡ ዘውእቱ ፡ ብሂል ፡ ፩ዱ ፡ እም፪ቱ ፡ ዝንቱ፡ ውእቱ ፡ አምላክ ፤ ወውእቱ ፡ ሰብእ ። ኤር፡፲፯ ፡ ፱ ።

## ዘኤጲፋንዮስ ፡ ም ፡ ፶፩ ።

፲፫ ሕፃን ፡ አበ ፡ እመ ፡ ማለትን ፡ ከማወቅ ፡ አስቀድሞ ፡ የደማስቆን ፡ ገንዘብ ፤ የሰማርያን ፡ ምርኮ፡ እንዲቀበል ፡ እግዚአብሔር ፡ በነቢዩ ፡ አድሮ ፡ ተናገረ ። ኢሳ ፡ ፰ ፡ ፬ ።

፲፬ ለሰው ፡ ዕውቀትን ፡ የሰጠ ፤ ለሰው ፡ ጆሮችን ፡ የፈጠረ ፤ የሰውንም ፡ አነጋገር ፡ ያከናወነ ፤ የዲዳዎች ፡ አንደበት ፡ እንዲናገር ፡ ያደረገ ፡ ጠቢብ ፡ እርሱ ፡ ስለእኛ ፡ ይህን፡ ሁሉ፡ ሥራ ፡ ገንዘብ፡ አደረገ፡ ስለእኛ ፡ ያደረገውን ፡ ይህን ፡ የሰውነት ፡ ሥርዓት፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ ። መዝ ፡ ፺፬ ፡ ፰—፲ ። ማቴ ፡ ፲፪ ፡ ፳፪—፳፬ ።

፲፭ ከእውነት ፡ ምሳሌዎች ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ አስማምተን ፡ ከሰበሰብናቸው ፤ በጎ ፡ ምሥጢርን፡ካወቅንባቸውና ፡ ገንዘብ ፡ ከአደረግናቸው ፡ ምስክሮች ፡ ምንም ፡ ምን ፡ አላስቀረም ፤ ያለ ፡ ትርጓሜ፡ ሃይማኖትን ፡ ለመቃወም ፡ በሚከራከሩን ፡ ሰዎች ዘንድ ፡ ተረት ፡ እንዳይሆን ። ዮሐ ፡ ፲፱ ፡ ፴፩ ።

፲፮ ከመጻሕፍት ፡ ቃላት ፡ እያንዳንዱን ፡ ቃላት ፡ በውስጣቸውም ፡ ያለውን ፡ ምሥጢር ፡ እናስተውል፤ ሰው ፡ እንደ፡ መሆኑ፡ የተናገሩለትን ፤ የነገሩንም ፡ ምክንያት ፡ ዳግመኛ ፡ እንናገር ። ዮሐ ፡ ፰ ፡ ፴፱ ።

፲፯ ይኸውም ፡ ፈጣሪያችሁ ፡ ነው ፤ እነሆ ፡ አምላኪየ ፡ ያለበትን ፡ ነገር ፡ አስቀድመን ፡ መላልሰን ፡ ተናግረናል ፤ ሰው ፡ እንደሆነ ፡ የሚያውቀውም ፡ እንደሌለ ፡ የተናገረለትን ፡ ያንዱን ፡ ቃል ፡ መንገድ (ምሥጢር( ፡ ዕውቀት ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡

፲፰ በዚህም ፡ በቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ቃል ፡ እርሱ ፡ ከሚታየውና ፡ ከማይታየው ፡ ከሁለቱ ፡ አንድ ፡ አካል አንድ ፡ ባሕርይ ፡ እንደሆነ ፡ ይታወቃል ፤ ስለ ፡ ክበበ ፡ ትስብእት ፡ አምላኪየ ፡ አለ ፡ ስለ ፡ መለኮት ፡ አባቴ ፡ አለ ።

፲፱ አባቴ ፤ አምላኪየ ፡ ስለ ፡ አላቸው፡ ስለ ፡ እነዚህ፡ ምሥጢራት ፡ መልስ ፡ ሊሰጥ ፡ የሚችል ፡ የለም ፤ ፍጡር ፡ ያይደለ ፡ ሰው ፡ እንደምን ፡ ያለ ፡ ነው ? ሰውስ ፡ ካልሆነ ፡ እንዴት ፡ ሰው ፡ ይባላል ?።

፳ የሚወለድ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ስሙ ፡ ከእናትና ፡ ከአባቱ ፤ ከዘመዶቹ ፤ከቤተ ፡ ሰቦቹ፡ከወገኖቹ፤ ከጐረቤቶቹ ፡ ከሀገሮቹ ፡ ሰዎች ፡ ይታወቃልና ፤ (ይህ ፡ሰው፡ የሆነ ፡ አምላክ ፡ መባል፤) ለዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ሊነገር አይገባም ፤ ይህ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይነገራል ፤ በእግዚአብሔር ፡ቃል ፡ ይፈጸማል ፡ እንጂ ።

፳፩ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ እንደሆነ ፡ ቢነገርም ፡ በውነት፡ ሰው ፡ ሆኗል ፤ አምላክ ፡ እንደ ፡ መሆኑም፡ያውቀው፡ ዘንድ ፡ የሚቻለው ፡ ሰው ፡ የለም ፤ ስለዚህም ፡ አብሲማዳኮስ ፡ ተባለ ፤ ይኸውም ፡ ከሁለት ፡ አንድ ፡ የሆነ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ እርሱ ፡ አምላክ ፡ ነው ፤ ሰው ነው ። ኤር ፡ ፲፯ ፡ ፱ ።

ዘኤጲፋንዮስ ፡ ም ፡ ፶፭ ።

፰፤ ወከማሁ ፡ ኮነ ፡ እሙነ ፡ እስመ ፡ ነፍስ ፡ ምስለ ፡ መለኮት ፡ ወረደት ፡ ውስተ ፡ሲኦል ፡ ወእምነ ፡ ሥጋሁ ፡ ኢተፈልጠ ፡ መለኮት ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ ውስተ ፡ መቃብር ፡ ሠሉሰ ፡ መዋዕለ ፡ ከመ ፡ ይክሥት ፡ ጽድቀ ፡ ትሥጉቱ ፡ ቅዱስ ፡ እስመ ፡ መለኮት ፡ ወነፍስ ፡ ፈጸሙ ፡ ምሥጢረ ፡ በውስተ ፡ሲኦል ፤ ወኢተእኅዙ ፡ ውስቴቱ ።

፱፤ ወበእንተ ፡ ዝንቱሂ ፡ ስምዕ ፡ ዘይብል ፡ እስመ ፡ ግዑዝ ፡ ውእቱ ፡ ውስተ ፡ ምውታን ፡ ወኢተሠልጠ ፡ ቦቱ ፡ ግብርናት ፡ በውስተ ፡ሲኦል ፡ በፈቃዱ ፡ ወረደ ፡ ውስተ ፡ ሲኦል ፡ በነፍሱ ። መዝ ፡ ፹፰ ፡ (፹፯) ፭ ።

፲ ጴጥሮስኒ ፡ ሐዋርያ ፡ ይብል ፡ እስመ ፡ ኢይክል እኂዞቶ ፡ ሞት ፡ ወዓዲ ፡ እግዚእነሂ ፡ መድኅን ፡ ይቤ ፡ ብየ ፡ ሥልጣን ፡ አንብራ ፡ ለነፍስየ ፡ ወአንሥአሂ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ ኖላዊ ፡ ኄር ፡ ወእሜጡ ፡ ነፍስየ ፡ ቤዛ ፡ አባግዕየ ። ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፲፩—፲፱ ። ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፪ ፡ ፳፬ ።

፲፩፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ተከዘት ፡ ነፍስየ ፡ እስከ ፡ ለሞት ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ምንተ ፡ እብል ፡ አባ ፡ አድኅና ፡ ለነፍስየ ፡ እምዛቲ ፡ ሰዓት ፡ ወባሕቱ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ መጻእኩ ፡ ወበጻሕክዋ ፡ ለዛቲ ፡ ሰዓት ። ማቴ፡ ፳፮ ፡ ፴—፴፱ ። ዮሐ ፡ ፲፪ ፡ ፳፯ና ፡ ፳፰ ።

፲፪፤ ወበዝንቱ ፡ ነገር ፡ ከሠተ ፡ ከመ ፡ መለኮት ፡ መጽአ ፡ በፈቃዱ ፡ በእንተ ፡ ዛቲ ፡ ሰዓት ፡ ወበትካዝሂ ፡ ዘተከዘ ፡ አዖቀ ፡ ጽድቀ ፡ ትስብእቱ ፡

፲፫፤ እስመ ፡ ከመ ፡ ንጉሥ ፡ ዐቢይ ፡ ዘቦቱ ፡ ፀብእ ፡ ምስለ ፡ ዘይቴሐቶ ፡ ወየአምር ፡ ዝኩ ፡ ንጉሥ ፡ ዐቢይ ፡ ከመ ፡ ጸላዒሁ ፡ ይትመዋዕ ፡ ወበተመውኦቱ ፡ ይማስና ፡ አህጉር ፡እንተ ፡ የኀልፍ፡ ዲቤሆን ፡ ወበጥበቡ ፡ ዝኩ ፡ ንጉሥ ፡ ዐቢይ ፡ ረሰየ ፡ ርእሶ ፡ ከመ ፡ ዘይትመዋዕ ፡ እስከ ፡ መሰሎ ፡ ለጸላዒሁ ።

፲፬፤ ወውእቱሰ ፡ ሶበ ፡ ርእየ ፡ ዘንተ ፡ አሕድአ ፡ ሐሊናሁ ፡ ወተአመነ ፡ በርእሱ ፡ ወእምዝ ፡ ተመይጠ፡ ንጉሥ፡ ዐቢይ ፡ ኀበ ፡ እማንቱ ፡ አህጉር ፡ ወአግብአን ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ ወለውእቱኒ ፡ መስተቃርን፡ አኀዞ ፡ ወበርበረ ፡ ኵሎ ፡ ንዋዮ ፡ ወአብጠለ ፡ ኵሎ፡ ግብሮ ፡ ኢያ ፡ ፰ ፡ ፩—፴ ።

፲፭፤ ወከማሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢፈርሀ ፡ እምነ ፡ ሞት ፤ እስመ ፡ ነገሮሙ ፡ ቀዲሙ ፡ ለአርዳኢሁ ፡ እንዘ ፡ ሀለዉ ፡ ምስሌሁ ፡ በፍኖት ፡ ወይቤሎሙ ፡ እስመ ፡ ወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ይገብዕ ፡ ውስተ፡እደ፡ሰብእ ፡ ኃጥአን። ወይሰቀል፡ ወይትቀተል፡ ወይትነሣእ፡እሙታን፡በሣልስት፡ለለት። ማቴ፡፳ ፡፲፯-፳

ዘኤጲፋንዮስ ፡ ም ፡ ፶፭ ።

፰፤ ዳዊት ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ እውነት ፡ ሆነ ፤ ነፍስ ፡ መለኮትን ፡ ተዋሕዳ ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ወርዳለችና፡ ሥጋም ፡ ሦስት ፡ መዓልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በመቃብር ፡ ሳለ ፡ መለኮት ፡ ከሥጋ ፡ አልተለየም ፡ አምላክ ፡ ሰው፡ የመሆኑን ፡ እውነትነት ፡ ያስረዳ ፡ ዘንድ ፡ መለኮትና ፡ ነፍስ ፡ በሲኦል ፡ ምሥጢርን ፤ ፈጽመዋልና ፤ በሲኦልም ፡ በቍራኝነት ፡ አልተያዙምና ።

፱፤ ስለዚህም ፡ ከሙታን ፡ ገብቶ ፡ እንደ ፡ ተቈጠረ ፡ በሲኦልም ፡ ቍራኝነት ፡ እንዳልሠለጠነበት ፡ በፈቃዱ ፡ በነፍስ ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ እንደ ፡ ወረደ ፡ የሚናገር ፡ ምስክር ፡ አለ ። መዝ ፡ ፹፰ ፡ (፹፯) ፭ ።

፲፤ ሐዋርያ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሞት ፡ ይዞ ፡ ሊያስቀረው ፡ አይችልም ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ፡ ጌታችን ፡ መድኃኒታችንም፡ ሰውነቴን፡ እጥላት፡ ዘንድ አስነሣት፡ ዘንድ፡ ሥልጣን ፡ አለኝ ፡ ብሏል ፤ ዳግመኛም ፡ ቸር ፡ ጠባቂ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ ለምእመናንም ፡ ቤዛ ፡ አድርጌ ፡ ሰውነቴን ፡ ለሕማም ፡ ለሞት ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለሁ ፡ አለ ። ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፲፩—፲፱ ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፪ ፡ ፳፬ ።

፲፩፤ ዳግመኛ ፡ ነፍሴ ፡ ለሞት ፡ እስከ ፡ መድረስ ፡ ደርሳ ፡ አዘነች ፤ ዳግመኛ ፡ አባቴ ፡ ሰውነቴን ፡ ከዚህች ፡ ሰዓት ፡ አድናት ፡ እላለሁ ፡ እንጂ ፤ ምን እላለሁ?አለ፡ነገር፡ ግን፡ ስለዚህ፡ሰው፡ ሆንኩ፤ከዚህችም ሰዓት፡ ደረስኩ።ማቴ፡፳፮፡፴—፴፱።ዮሐ፡፲፪፡፳፯ና፳፰።

፲፪፤ በዚህም ፡ አነጋገር ፡ መለኮት ፡ በፈቃዱ ፡ በዚች ፡ ሰዓት ፡ መከራ ፡ ለመቀበል ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ አስረዳ ፤ በአደረገው ፡ ኃዘንም ፡ ሰው ፡ የመሆኑን ፡ እውነትነት ፡ አስረዳ ።

፲፫፤ ከወሬኛ ፡ ጠላት ፡ ጋር ፡ ፀብ ፡ እንዳለው ፡ ገናና ፡ ንጉሥ ፡ ያ ፡ ገናና ፡ ንጉሥ ፡ ጠላቱ ፡ ድል ፡ እንዲሆን ድል ፡ በመሆኑም፡ የሚዘምትባቸው፡አገሮች ፡ እንዲጠፉ ፡ ያውቃል ፤ ነገር ፡ ግን ፤ ያ ፡ ገናና ፡ ንጉሥ፡ በጥበቡ ፡ ራሱ ፡ ድል ፡ እንደ ፡ ተነሣ ፡ አደረገ ፤ ለጠላቱ ያ ፡ ገናና ፡ ንጉሥ ፡ እርሱን ፡ ከመፍራት ፡ የተነሣ ፡ ድል ፡ የተነሣ ፡ እስኪመስለው ፡ ድረስ ።

፲፬፤ ጠላቱም ፡ ይህን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ተዘለለ ፤ በኀይሉም ፡ ታመነ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያ ፡ ገናና ፡ ንጉሥ ፡ ወደነዚያ ፡ አገሮች ፡ ተመለሰና ፡ እጅ ፡ አደረጋቸው ፤ ጠላቱንም ፡ ያዘው ፤ ገንዘቡንም ፡ በረበረው ፤ ሥራውንም ፡ ሁሉ ፡ አጠፋ ። ኢያ ፡ ፰ ፡ ፩—፴ ።

፲፭፤ እንደዚሁም ፡ ሁሉ ፡ ጌታችን ፡ ሞትን ፡ አልፈራም ፤ በቢታንያ ፡ ጕዳና ፡ ሳሉ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ አስቀድሞ ፡ ነግሮዋቸዋልና ፡ ወልደ ፡ እጓለ፡ እመሕያው ፡ ክርስቶስ ፡ በኃጥአን ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ ይያዛል ፤ ይሰቀላል ፤ ይሞታል ፤ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ ይነሣል ፡ ብሏቸዋልና። ማቴ ፡ ፳ ፡ ፲፯—፳ ።

